ቆሻሻን መጣያ ጣቢያ ሚዛኖች እና የሚዛን ቤት (Scale House ) በመቀየር እየተሰራ ባለው ፕሮጀክት፤ ጊዜያዊ ቆሻሻ መጣያ ጣቢያ (Transfer Station) አሰራር
እና ለተሽከርካሪዎች የሚውል የቆሻሻ መጣያ ክፍያ መርሃ ግብር፥

**ማጠቃለያ :** ከጃንዋሪ 2፣ 2024 ጀምሮ፣ እስከ ጥቅምት 31፣ 2024 ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአካባቢ ጥበቃ ዲፓርትመንት (DEP) የካውንቲውን የቆሻሻ መመዘኛ (ስኬልስ- scales) ለመቀየር እየተሰራ ባለው የግንባታ ስራ፣ በካውንቲው ሼዲ ግሮቭ ቆሻሻ መጣያ ጣቢያ፣ ጊዜያዊ የቆሻሻ መጣያ ክፍያ (tipping fee) መርሃ ግብር ተግባራዊ ያደርጋል። በተለይም ይህ ጊዜያዊ የክፍያ መርሃ ግብር በ ዲኢፒ(DEP) ሰነድ ላይ የእነዚህ ተሽከርካሪዎች የባዶ ክብደት ("ታሬ ክብደት") ላልተመዘገቡ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ይሆናል።

የቆሻሻ መመዘኛ ግንባታ ፕሮጀክት በሚካሄድበት ወቅት አነስተኛውን የቆሻሻ መጣያ(the annex) የሚጠቀሙ ሁሉም ተሽከርካሪዎች በሙሉ ሚዛናቸውን አልፈው ክፍያቸውን ይፈጽሙና በፍሬድሪክ ሮድ/Frederick Road (355) መውጫን በመጠቀም ይወጣሉ። ለሚጣለው ቆሻሻ የሚከፈለው ክፍያ ከእዚህ በታች በተገለጸው የአማካይ ክፍያ ተመን እና በተሽከርካሪው አይነት መሰረት ይሆናል። አካውንት ወይም የመክፈያ ምዝገባ ለሌላቸው / ኮንትራክተርስ/ ነዋሪዎች / የመሬት ገጽታ እና ግንባታ ኩባንያዎች 2 አማራጮች ይኖራሉ።

**<u>አማራጭ 1</u>** - ከኖቬምበር 1፣ 2023 በኋላ፣ ባዶ (ታሬ) ክብደትን ለመመስረት የሚጠቅመውን የክብደት ካርድ ለመሙላት የሚዛን ቤቱ (scale house) ክፍት ይሆናል። በጃንዋሪ 2፣ 2024 እና ጥቅምት 31፣ 2024 መካከል ወደ ቦታው ሲገቡ የሚከፈለውን ክፍያ ለማስላት ባዶው ክብደት መሰረታዊ ክብደት (ታሬ ክብደት) ተደርጎ ይወሰዳል።

**<u>አማራጭ 2</u>** - ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ የተቀመጡት ክፍያዎች በተሽከርካሪው ዓይነት ላይ ተመስርተው ተግባራዊ ይሆናሉ። እነዚህ የክፍያ መጠኖች በሚዛን ቤቱ ባዶ (ታሬ) ክብደት ላልተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ይውላል።

| በሚዛን ጥገና ጊዜ ለተወሰኑ ተሽከርካሪዎች የሚውል ጊዜያዊ የቆሻሻ መጣያ ክፍያ ተመን | | |
|---|---|---|
| የተሽከርካሪ አይነት | የቆሻሻው ዓይነት | ቆሻሻ መጣያ ክፍያ ተመን (ከጁላይ 1፣ 2022 እስከ ጁን 29፣ 2023 በተከፈለው አማካይ የቆሻሻ መጣያ ክፍያ መሰረት) |
| ፒካፕ ወይም ቫን -ካለ ተጎታች (Pick-up and Vans (no trailer)) | MSW-190 | $28.91 |
| | C&D-191 | $39.46 |
| | DOT-1005 | $48.64 |
| | YW-106 | $24.21 |
| ፒካፕ ወይም ቫን ከተጎታች ጋር (Pick-up or Van with Trailer)<br>እና<br>ስቴክ ቦዲ/ስሞል ሬንታል ደምፕስ (Stake Body/Small Rental Dumps) | MSW-190 | $54.71 |
| | C&D-191 | $70.19 |
| | DOT-1005 | $107.09 |
| | YW-106 | $38.39 |
| ማስታወሻዎች:-<br>ከ 500 ፓውንድ በታች ለሆኑ "ቀላል ጭነቶች" የቆሻሻ መጣያ ክፍያ አይከፈልም።<br>"MSW" - የማዘጋጃ ቤት ደረቅ ቆሻሻ<br>"C&D" - የግንባታ እና የፍርስራሽ ቆሻሻ<br>"DOT" - የመጓጓዣ ቆሻሻ መምሪያ<br>"YW" - የአትክልትና እፅዋት ቆሻሻ | | |

ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን የሚዛን ቤቱን ተቆጣጣሪ ለማነጋገር ይጠይቁ።